# የአፍሪካ ቀንድ፤ ከታላቅነት ወደ ውድቀት፤ እና ተስፋ?

ኪዳኔ ዓለማየሁ::

1. *መግቢያ*

1.1 የዚህ ጽሑፍ መሠረታዊ ሀሳብ የአፍሪካ ቀንድ ሐገሮች ልማትና ሰላም ሊያገኙ የሚችሉት በሕብረት እንጂ በነጠላ ሊሆን እንደማይችል ለማመልከት ነው። ለዚህም በዋቢነት የአፍሪካ ቀንድ፤ አንድነት በነበረው ዘመን ራሱን የቻለ ሀያል መንግሥት እንደ ነበረ፤ ከተከፋፈለ በሁዋላ ግን ድከመትና ድሕነት እያጠቁት መሆኑን ከታሪክ መረጃ አቀርባለሁ። አሁን ባጭሩ የማቀርበው ሐተታም "የአፍሪካ ቀንድ፤ ከታላቅነት ወደ ውደቀት፤ እና ተስፋ?" በእንግሊዝኛ "Horn of Africa: from Glory to Misery, and Hope?" ከተሰኘው ጽሑፌ በመቀንጨብ ነው።

1.2 ጽሑፉ የሚያተኩረው በጠቅላላው በአፍሪካ ቀንድ በተለይ ግን በኢትዮጵያ ላይ ሲሆን፤ በመጀመሪያው ሺ ዘመነ-ምሕረት የት እንደ ነበርን፤ በሁለተኛው ሺ ዘመነ-ምሕረት የት እንደ ደረስን እንዲሁም በሶስተኛው ሺ ዘመን ስላለን ተስፋ ይጠቁማል።

1.3 መስፍን ወልደማርያም "Horn of Africa: Conflict and Poverty" በተሰኘ መጽሐፉ የአፍሪካ ቀንድ ዋነኛ ("principal") ሐገሮች ኢትዮጵያ፤ ኤርትራ፤ ሱማሊያ እና ጅቡቲ ናቸው ይላል። ሌሎች ምንጮች የአፍሪካን ቀንድ ተለቅ እያደረጉ ሱዳንን፤ ኬንያን፤ ቡሩንዲን፤ ዩጋንዳንና ሩዋንዳን ይጨምራሉ። መስፍን ወ/ማርያም እነዚህን ሐገሮች የዳር ("peripheral") ይላቸዋል። እነዚህ ሐገሮች በሌሎች ስብስቦች ውስጥ ስለሚሳተፉ ይህ ንግግሬ የሚያተኩረው ዋነኛ በተባሉት በኢትዮጵያ፤ በኤርትራ፤ በሱማሊያና በጅቡቲ ብቻ ይሆናል።

2. *የአፍሪካ ቀንድ በመጀመሪያው ሺ ዘመነ-ምሕረት*

2.1 በእነሥርግው ሐብለሥላሴ፤ ታደሰ ታምራት፤ ዳንኤል ክንዴ፤ E. Naville, H.von Wissman, S.B.Miles, Donald Levine, Richard Pankhurst, Sven Rubensen, Mani, እና ሌሎችም ጸሐፊዎች እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርዓን እንደተዘገበው የአፍሪካ ቀንድ ኢትዮጵያ በመባል ሲታወቅ በጊዜው ከነበሩት ሶስት ሐያላን መንግሥታት አንዱ ነበር። ሌሎቹ ፋርስ (ያሁኑዋ ኢራን) እና ቢዛንቲየም ነበሩ። በዚያን ጊዜ ጂቡቲ፤ ኤርትራ እና ሱማሊያ የሚባሉ ሐገሮች አልነበሩም።

2.2 በዚያን ዘመን፤ ኢትዮጵያ የአፍሪካን ቀንድ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ እስከ ግብጽ ድንበር እንዲሁም የመንን እና ዛሬ ሳውዲ ዓረቢያ ውስጥ የሚገኙትን መካን፤ ናግራን፤ ጃእፈርንና አካባቢዎቹን ትቆጣጠር ነበር። (አባሪ የሆነውን ማፕ ይመልከቱ።)

2.3 እንደ ዛሬዋ አሜሪካ፤ በዚያን ጊዜ የስደተኞች መሸሸጊያ ኢትዮጵያ ነበረች። ለዚያ ነበረ፤ የመጀመሪያዎቹ እስላሞች መካ ውስጥ ጥቃት ሲደርስባቸው፤ ነቢያቸው መሐመድ ወደ

ኢትዮጵያ እንዲሰደዱ የመከራቸው። ከ100 በላይ የተቆጠሩት ስደተኞች፤ የነቢዩ ልጅ ሮኬያና ባለቤትዋ ኦትማን ጭምር፤ 15 አመት ሙሉ አክሱም ተጠልለው ወደ ሐገራቸው ተመልሰዋል።

2.4 ሌላም እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ የሚገባው በአጼ ካሌብ ዘመነ መንግሥት የተከናወኑት ሁለት ዘመቻዎች ናቸው። እ.ኤ.አ. በ523-525 ኢትዮጵያ የራስዋን 70 ትልልቅ እና 100 ትንንሽ መርከቦች እንዲሁም ከሌሎች አካባቢዎች የተገኙ 60 በጠቅላላው 230 መርከቦች አዘጋጅታ ከ70፣000 እስከ 120፣000 የተገመተ ጦር ናግራንና ጃእፈር በተሰኙ ዛሬ ሳውዲ ዓሬብያ ውስጥ በሚገኙ ስፍራዎች 3፣000 ክርስቲያኖች (ኢትዮጵያውያንን ጭምር) በጨፈጨፈው እምነቱን ወደ አይሑዳዊነት በለወጠ ዓረብ ዘምተውበት ተቆጣጥረውት ነበር።

2.5 ሌላው በዚያ ዘመን የተከናወነ የኢትዮጵያንና የአፍሪካ ቀንድን ሐያልነት የሚያረጋግጥ ክስተት እ.ኤ.አ. በ570 ሰንዓ፤ የመን የነበረው የኢትዮጵያ ክፍለ ጦር በዝሆን ታጅቦ ወደ መካ የዘመተው ነው። ስለዚህ ዘመቻ ዓረቦች ዘግበው እስካሁን ለልጆቻቸው የሚነግሩትና እነሥርግው ሐብለሥላሴ የሚሉት የተለያየ ነው። በዓረቦቹ በኩል ተጽፎ የሚገኘው፤ በአብርሃም የሚመራው ጦር መካ ሲደርስ ሰማዩ በወፎች እንደ ተሸፈነና እያንዳንዷም ወፍ በአፏና በእግሮቿ የያዘቻቸውን ጠጠሮች ስትለቅ የኢትዮጵያ ጦር እንደ ተደመሰሰና የቀረው ሸሽቶ ሰንዓ ተመለሰ የሚል ነው። ሥርግው እንደጻፈው ግን የኢትዮጵያ ጦር በኩፍኝ ተላላፊ በሽታ እንደ ተጠቃና መካም በነበረበት ጊዜ የሚቋቋመው ሐይል እንዳልነበረ ነው።

2.6 በመጀመሪያው ሺ ዘመን ኢትዮጵያ በጦር ሐይል ብቻ ሳይሆን በንግድ፤ በስነ-ጽሑፍና በሌሎች በባሕላዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች እጅግ የተደነቀና የተከበረ ስፍራ ነበራት። ክርስትናና እስላም ሃይማኖቶች አፍሪካ ቀንድ የገቡት ቀደም ብለው ሲሆን እንደ ሌሎች ሐገሮች በግዳጅ ሳይሆን በውዴታ ነበር።

2.7 ወደ የመጀመሪያው ሺ ዘመን መገባደጃ፤ በሁለት ዋና ምክንያቶች፤ የኢትዮጵያ ሐያልነት እየመነመነ ሔደ። እነዚህም የአክሱም መንግሥት ከውስጥ መዳከም እና በፋርስ እርዳታ ኢትዮጵያ ከየመን ከተወገደች በኋላ በእስልምና አማካኝነት ዓረቦች በመጠናከራቸው ነው።

3. <u>በ2ኛው ሺ ዘመንስ ምን ተከሰተ?</u>

3.1 ምንም እንኳ በ13ኛው ምእት ዓመት እነንጉሥ ዳዊት ወደ ሰሜን እስከ ግብጽ ወደ ምሥራቅና ደቡብ በየአቅጣጫው የኢትዮጵያን ግዛት ቢያስፋፉትም ሁለተኛው ሺ ዓመት የአፍሪካ ቀንድ በአጠቃላይ የተቀነባጠበበት ዘመን ነው።

3.2 መጀመሪያ የኦቶማን መንግሥት በቀይ ባሕር በኩል ያለውን የኢትዮጵያን ግዛት ያዘች። ግብጽም ኢትዮጵያ ውስጥ ዘልቃ ሐረርን እስከ መያዝ ደረሰች። ግብጽ ከምታገኘው ውሀ 86% የሚፈስላት ከኢትዮጵያ በመሆኑ የውሀ ምንጯን ለመቆጣጠር ከአስር ጊዜ በላይ አትዮጵያን ለመውረር ሞክራ ሳይሳካላት ቀረ።

3.3 በ19ኛው ምእት ዓመት ኦቶማኖችና ግብጾች በአውሮፓ ኮሎኒያሊስቶች ተተኩና እንግሊዞች፤ ፈረንሳዮችና ኢጣሊያኖች ባሕረ ነጋሽን (በኋላ ኤርትራ ብለው የሰየሙትን)፤ ጅቡቲንና

ሱማሊያን ተከፋፍለው ያዙ።

3.4 የቀረውም የኢትዮጵያ ግዛት በኮሎኒያሊስቶች በተለይም በኢጣሊያ ሳይያዝ የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአድዋና በሌሎችም ጦርነቶች ባገኘው ድልና ባስመሰከረው ጀግንነት ነበር።

3.5 ቢሆንም፤ ከዚህ ቀጥሎ እንደማሳየው፤ በ2ኛው ሺ ዘመን መጨረሻ የአፍሪካ ቀንድ ሁኔታ እጅግ የሚያሳዝን ሆነ።

(ሀ) የአፍሪካ ቀንድ 4 እጅግ ደሀ የሆኑ በማንኛውም መስፈርት በዓለም በኋላ ቀርነት የሚታወቁ ሐገሮች የሚገኙበት አካባቢ ሆነ። ለምሳሌ፤ UNDP በየጊዜው በሚያወጣው የሰው ልጅ ልማት መስፈርት (Human Development Index)፤ ከ177 ሐገሮች፤ ኢትዮጵያ 170ኛ ስትሆን፤ ኤርትራ 161ኛ፤ ጂቡቲ 150ኛ፤ ሱማሊያ (አይታወቅም)። ሰፊ የውሀ፤ የእርሻ፤ የማእድን፤ የሰው ኃይል ያለው አካባቢ፤ በአገዛዝ ድክመት ምክንያት፤ ተመጽዋች፤ የረሐብና የሰቆቃ ሰለባ ሆኖ ቀርቷል።

(ለ) በአመራር ጉድለት ምክንያት ኢትዮጵያ ከኤርትራና ከሱማሊያ ጋር በተለያዩ ጊዜዎች ባደረገቻቸው ጦርነቶች በሙቶ ሺ የሚቆጠሩ ወንድማማቾች ተሰውተዋል። ይህ አልበቃ ብሎ አሁን ያለው ሁኔታ ኢትዮጵያ ሱማሊያን ወርራ ከወጣች በሁዋላ ከኤርትራ ጋር ለሌላ ዙር ጦርነት እየተዘጋጀች ነው ይባላል።

(ሐ) ድሕነቱ እንደ ወባና ኤች.አይ.ቪ. ኤይድስ ከመሳሰሉ ደዌዎች ጋር ተጣምሮ የአፍሪካ ቀንድን ሕዝብ እየጨፈጨፈው ነው።

(መ) በአፍሪካ ቀንድ በአራቱም ሐገሮች የተከሰቱት አገዛዞች ፍትሕና ዲሞክራሲ የሌላቸው፤ ጎሰኝነትና ዘረኝነት የተጠናወታቸው በመሆናቸው ሕዝቦቹ በጭቆና ስልት ፍዳቸውን እያዩ ነው። አንዱ የሌላውን ተቃዋሚ እያሰለጠነና እየረዳ አካባቢው ሰላመ-ቢስ ሆኗል። ባለፉት 30 ዓመታት የአፍሪካ ቀንድ የተማረው ነገር ቢኖር፤ መገነጣጠል፤ ዘረኛነት፤ በገዛ መሬቱ ጪሰኛ መሆኑ፤ ጭቆናና፤ ድሕነት ያንገፈገፉት መሆኑን ነው። ፕሮፌሰር አዱኛ ወርቁ “በቃ ተነስ ታገል” በተሰኘ ሲዲው “የትኛው ነው ዘሬ” በተባለው እንጉርጉሮው እንዲህ ብሏል፤

“በቆየ ታሪኩ በእምነት በባሕሉ
ሕዝቡ አንድ መሆኑን እያስተባበሉ
ነጻነት ነጻነት ነጻነት እያሉ
ከናት አገራቸው የተገነጠሉ
እንኩዋን ጤፍ እንጀራ አሮባቸው ስንዴ
ሁለት ያጣ ጎመን ሁነው የለም እንዴ
እውነት አይምሰልህ ልብ በል ወገኔ
መለያየት ሞት ነው ላንተም ሆነ ለኔ።”

ለዚሕ እውነት ምሥከሩ፤ የአፍሪካ ሲንጋፖር ትሆናለች ተብሎ የተገነጠለችው ኤርትራ በመማቀቅ ላይ የምትገኝ መሆኑ ነው።

ሎሪዬት ጸጋዬ ገብረመድህንም “Yes. We Betrayed our Ancestors” በተሰኘው ጽሑፉ እንደሚከተለው ዘግቧል፤

“It is, therefore, a matter of the utmost urgency;
A question of life and death,
To stand up together for the people of the Horn of Africa…
To reach out and grasp the higher dream of our ancestors,
To grasp the larger picture of peace, love and unity,
Now, before it is too late for all of us.
When our fathers gave us the cradle of the First World,
At the beginning there was KA, the first God of Earth and Sky;
On this birth land of our first ancestors.
They raised for us the sacred shrine
On the glowing head piece of the Horn of Africa,
Where the sun first touched the body of the Earth,
But, alas, now, look at us!
The generation who has forgotten how to unite,
The rotten link that has lost the scale of self-respect,
Look at us!”

(ሠ)በአፍሪካ ቀንድ፤ 2 የሐያላን ሐገሮች ጦሮች ይገኛሉ። እነርሱም፤ የአሜሪካና የፈረንሳይ ሲሆኑ ጂቡቲ ይገኛሉ። እዚያ የሚገኙትም ለአፍሪካ ቀንድ ጥቅም አይደለም።“Arms for the Horn” በተሰኘ መጽሐፉ Jeffrey A. Lefebvre (ጄፍሪ ኤ. ለፌቭረ) ለአሜሪካ፤ የአፍሪካ ቀንድ ከሳውዲ ዓረቢያ ባሻገር ከመገኘቷ ሌላ ምንም ዋጋ የላትም ይልና ባካባቢው አሜሪካ የምታተኩርባቸውን ጥቅሞች ይዘረዝራል፤

(1)በቀይ ባሕር ያለውን መመላለሻ መጠበቅ፤
(2)ከደቡብ በኩል የሚፈስላት ውሀ እንዳይነካ ግብጽን መደገፍ፤
(3)ሳውዲ ዓረቢያንና በአካባቢው ያሉትን የአሜሪካ ወዳጆች ከሚያቃውስ ተግባር መጠበቅ። በተጨማሪ፤ ሊጠቀስ የሚገባው በዛሬው ጊዜ፤ አሜሪካ ከዓለም አቀፍ ነውጠኞች ጋር አከናውናለሁ የምትለውን ትግል በአፍሪካ ቀንድ ትኩረት የሚገባው ወይም አንገብጋቢ ጉዳይ አድርጋ ትቆጥራለች።

(ረ)በአጠቃላይ፤ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በአንደኛው ሺ በአንድነቱ ተከብሮ የነበረውን ያህል በሁለተኛው ሺ መጨረሻ ደካማና እርስ በርስ እየተናቆረ የሚጨራረስ ተመጽዋች ሆኖ ይገኛል። ሐያላን መንግሥታትም ለጥቅማቸው የሚበጅ እየመሰላቸው፤ አካባቢው ተዳክሞና ተገነጣጥሎ እንዲቆይ እያደረጉ ነው። ራሱን ማዳን የሚችለው የአፍሪካ ቀንድ ሕዝብ ራሱ ብቻ ነው።

4. <u>በ3ኛው ሺ ዘመንስ ምን ዓይነት ተስፋ ሊኖር ይችላል?</u>

4.1 በ3ኛው ሺ መጀመሪያ ላይ የሚታየው የአፍሪካ ቀንድ ሁኔታ እጅግ ዘግናኝ ቢሆንም ተስፋ የሚሰጡ ብዙ እሴቶችም አሉት፤

(ሀ)100 ሚሊዮን የደረሰው ሕዝብ፤ (ኢትዮጵያ 85ሚሊዮን፤ ሱማሊያ 10 ሚሊዮን፤ ኤርትራ 5 ሚሊዮን፤ ጇቡቲ 0.8 ሚሊዮን)፤
(ለ)እምብዛም ጥቅም ላይ ያልዋሉ እንደ ዓባይ ያሉ ወንዞች፤
(ሐ)ሰፊ የእርሻ ሐብት፤
(መ)የነዳጅና የማእድን ሐብት፤
(ሠ)ሰባት በቀይ ባሕር፤ በኤደን ሰላጤና በሕንድ ውቅያኖስ የሚገኙ ወደቦች፤
(ረ)ለዓለም ከፍተኛ የትራንስፖርት ጥቅም የሚያስገኘው ቀይ ባሕር፤
(ሰ)ዋና የነዳጅ አምራች ሐገሮች ጉርብትና በመኖሩ በቀይ ባሕር አካባቢ ያሉ ሐገሮች የሕብረትና የልማት ማእከል አቋቁመው ሊጠቃቀሙ ስለሚችሉ፤
(ሸ)የታሪክ፤ የባሕልና የኤኮ-ቱሪዝም ሐብት፤
(ቀ)የአሕጉራዊ ድርጅቶች፤ ማለት፤ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፤ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽንና ኢጋድ ዋና መሥሪያ ቤቶች የሚገኙበት በመሆኑ፤
በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና ሕብረት ቢከሰት ፈጣን ልማት ሊገኝ እንደሚችል የታወቀ ነው።

4.2 በ3ኛው ሺ ዘመን በአፍሪካ ቀንድ መስፈን የሚገባቸው ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1ኛ/ ጭቆናን፤ ዘረኛነትን፤ መገነጣጠልን፤ ድህነትን፤ ድንቁርናን፤ እርስ በርስ መጋጨትንና መናቆርን እንዲሁም አስከፊና አመንማኝ የሆነውን ሙስና ሁሉ አስወግዶ በዲሞክራሲ፤ በሰላም፤ በልማት፤ በግልጽነትና፤ ቁጥጥር በሰፈነበት ሁኔታ የሚተካ ዘመናዊ አመራር ለአፍሪካ ቀንድ ያስፈልጋል።

2ኛ/ ሰላምና የተፋጠነ ልማት የሰፈነበት ሁኔታ ማስገኘት የሚችል አመራር ከተገኘ በአፍሪካ ቀንድ በመጀመሪያ ደረጃ በኮንፌደሬሽን ቀጥሎም በፌደሬሽን ወይም ስምምነት ከተገኘ፤ በቀጥታ በፌዴሬሽን፤ የተሙዋላ ሕብረት መፍጠር ያስፈልጋል። ከዚህም ጋር ጠቅላላውን የአፍሪካን ሕብረትና አንድነት ዓላማ ማጠናከርና መተግበር ይገባል። በዚህ አጋጣሚ፤ ስለ አ ፍሪካ ቀንድ ኮንፌዴሬሽን ጉዳይ፤ ታምፓ፤ ፍሎሪዳ፤ አሜሪካ፤ አንድ ዓለም-አቀፍ ጉባዔ ተከናውኖ የተገኘውን ውጤት www.hafrica.comን ድረ-ገፅ በመጎብኘት “Tampa Declaration” የተሰኘውን ሰነድ መመልከት ይቻላል።

3ኛ/ ከ20 ዓመት በሁዋላ የሕዝቡ ቁጥር ወደ 140 ሚሊዮን የሚደርሰው የአፍሪካ ቀንድ ክፍለ-አሕጉር፤ ሕብረቱንና ልማቱን ካጠናከረ የቀይ ባሕር አካባቢ ሐገሮችን፤ እሥራኤልንና በባሕሩ ዙሪያ ያሉትን የዓረብ ሐገሮች ጨምሮ ለልማት የሚያስተባብር ማእከል ማቋቋም ይቻላል። በነዳጅ ሐብት የከበሩት የዓረብና ሌሎችም የእስላም ሐገሮች ለአፍሪካ ቀንድ የውሀና የእርሻ ሐብት ጉጉትና ለሃይማኖት ማስፋፊያ ሲሉ የሚያከናውኑትን ጠባብና መሠሪ የሆነ ተጽእኖ ትተው ለሁሉም መጠቃቀም በሚቻልበት በኢኮኖሚ ልማት ሕብረት ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ ይቻላል።

4ኛ/ ዓለም-አቀፉ ሕብረተሰብም፤ በተለይም የአሜሪካና የፈረንሳይ መንግስቶች ስለ አፍሪካ ቀንድ አካባቢ እስካሁን የሚከተሉትን ጠባብ ስልት አሻሽለው ላሰማሩዋቸው ጦሮቻቸው በከንቱ የሚያባክኑትን ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር ሐብታቸውን ላካባቢውና ለራሳቸውም ለዘለቄታው በሚበጅ የልማት፤ የዲሞክራሲና የሕብረት ተግባር እንዲያውሉት ማድረግ ያስፈልጋል።

5ኛ/ ውጪ ሐገሮች የምንገኝ የአፍሪካ ቀንድ ዜጎችም ያካባቢው ሕዝብ ዲሞክራሲ፤ ሰላም፤ ልማትና ሕብረት እንዲከሰትለት ለማድረግ ከፍ ያለ ሚና ሊኖረን ይገባል። በአመራር ድክመት ምክንያት በአፍሪካ ቀንድ ያለውን መናቆር ውጪ ሐገርም በማንጸባረቅ ፈንታ ከኢትዮጵያ፤ ከኤርትራ፤ ከሱማሊያና ከጅቡቲ የመጣነው ሕዝቦች ለደህው ወገናችን በሚበጅ ስልት እንድንተባበርና በአካባቢው ሰላም፤ ልማትና ሕብረት እንዲከሰት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይገባናል። በዚህ ረገድ ለመሳተፍ የሚፈልግ ሰው፤ ከአፍሪካ ቀንድ ሰላምና ልማት ማእከል ጋር በመተባበር አስፈላጊውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል። የማእከሉን መተዳደሪያ ደንብ በwww.hafrica.com መመልከት ይቻላል።

5. <u>የአፍሪካ ቀንድ የሰላምና ልማት ማእከል (www.hafrica.com)</u>

5፣1 ማእከሉ የተቋቋመው በ2003 ሲሆን ራእዩም አራቱ የአፍሪካ ቀንድ ሐገሮች አንድነት መስርተው፤ ሰላምና ልማታቸውን አጠናክረው ሕዝቡ ከድሕነትና ከጭቆና ተላቆ ራሱን የቻለ፤ ዲሞክራሲ የሰፈነበት አካባቢ ሆኖ ለማየት ነው። የሚኪያሔደውም ከአራቱም አገሮች በተውጣጡ ሰዎች ነው።የማእከሉ ተልእኮ በአፍሪካ ቀንድ የጠነከረ ሰላምና ልማት በሚያስገኙ አርእስቶች ጥናቶች እየተከናወነ ጥልቀት ባለው ሁኔታ ውይይት ለማከናወንና በፍትሔዎቸ ለመጠቆም ነው።

5.2 ማእከሉ የተጠነሰሰው እ.ኤ.አ. በ2002 ታምፓ፤ ፍሎሪዳ፤ ከዩኒቨርሲቲ ኦፍ ሳውዝ ፍሎሪዳ ጋር በመተባበር ስለ አፍሪካ ቀንድ ኮንፌዴሬሽን በተከናወነው ዓለም አቀፋዊ ጉባዔ ላይ ነበር። በጉባዔው፤ 300 ተሳታፊዎች፤ ከብዙ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ምሑራን፤ ከአንዳንድ የተባበሩ መንግሥታት ድርጅቶች፤ ከስቴት ዲፓርትሜንት፤ ከዋይት ሐውስ የኤች.አይ.ቪ. ኤይድስ እርዳታ ማስተባበሪያ ክፍል እንዲሁም ከግብረ ሠናይ ድርጅቶች የመጡ አቅራቢዎች ነበሩ። ባጭሩ፤ የኮንፌዴሬሽኑ ጽንሰ ሀሳብ ክቡር ቢሆንም የሚያስፈልጉት ቅድመ ዝግጅቶችና ሁኔታዎች በጉባዔው ተዘርዝረው ተጠቁመዋል። ዝርዝሩን በwww.hafrica.com ድረ ገጽ “Tampa Declaration” በተሰኘው ጽሑፍ መመልከት ይቻላል።

5.3 እስካሁን ድረስ ማእከሉ ያከናወናቸው ተግባሮች፤

(1) በጥቅምት 1999 ዓ/ም ከዩኒቨርሲቲ ኦፍ ቴክሳስ አት አርሊንግተን ጋር በመተባበር ለአፍሪካ ቀንድ ስለሚያስፈልገው ልማት አንድ ዓለም አቀፋዊ ጉባዔ ዳላስ ተከናውኗል። በጉባዔውም ላይ የዓለም ባንክ፤ አንዳንድ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች፤ ከልዩ ልዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ምሑራን፤ ሌሎችም መንግሥታዊና የግብረ-ሠናይ ድርጅቶች ተወካዮች ተገኝተው ነበር። የጉባኤው ውጤት በዓለም ባንክና በኮሜሳ (Common Market for Eastern and Southern Africa) ድርጅቶች አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ እንዲሰራጭ ታቅዷል።

(2)በቅርቡ አንዳንድ ምሑራንን በመጋበዝ ስለ አፍሪካ ቀንድና በተለይም ስለ ሱማሊያ ጉዳዮች ውይይቶች እንዲከናወኑ ተደርጓል።

(3)ከዳላስ የሰላም ማእከል ጋር በመተባበር የሶማሊያ ጉዳይ ለሕዝቡ ሰላምና ልማት በሚያስገኝ ስልት እንዲከናወን ለሴኔተር ፋይንጎልድ የጥምር አቤቱታ ደብዳቤ ተልኳል።

(5)ኢጋድ፤ ካርቱም ላይ ባከናወነው ስብሰባ በመገኘት ለአፍሪካ ቀንድ ሰላምና ልማት ስለሚገኝበት ስልት ሀሳብ ቀርቧል።

5.4 የማእከሉ ያጭር ጊዜ ፕሮግራም፤

(1) በቅርቡ ስለ አፍሪካ ቀንድ የጤና ችግር ውይይት ይከናወናል፤

(2) እንዲሁም በአፍሪካ ቀንድ ግጭትን ስለ ማስወገድ (Conflict Resolution) አንድ ዓለም አቀፋዊ ስብሰባ ለማከናወን ታቅዷል።


6. <u>ማጠቃለያ</u>

1. በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና የተፋጠነ ልማት ለማስገኘት አራቱም ሐገሮች በሕብረት መጣር ያስፈልጋቸዋል።

2. የአፍሪካ ቀንድን ሕዝብ የሚያናቁረውና የሚያጋጨው መሠሪ የውጪ ፖለቲካ ተጽእኖና አጉል አመራር ነው እንጂ ባለው የስነልቦና፤ የባሕልና የስነፍጥረት ተቀራራቢነት በሰላምና በሕብረት አንድነቱንና ልማቱን ለማጠናከር የሚችል ነው።

3. ጥረቱን ለማቀናጀት የሚያመቻች ሕብረት፤ ግልጽ ራእይ፤ ጠንካራ አወቃቀርና የልማት ስልት ያስፈልጋል።

4. ሕብረቱ ዘላቂ ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው በአፍሪካ ቀንድ ዲሞክራሲና ፍትሕ ሲከሰቱ ነው።


The Empire of Ethiopia
According to Monumentum Adulitanum
AEGYPTUS
ARABIA
ARABICUS SINUS
BLEMENIA
NUBITIS
TAGUIEA
AXUMITES
AETHIOPIA
Sabaei
RAEIDAN
Bomeritae
Axum
Agame
Gaze
Sigyen
Metine
Zingabene
Atbagai
Gabala
Gambala
Sesea
Annine
(SASU)
Kalaa
Kbausae
Salate
Tribus circumvagntes Gentis
Adopted from
Rühl V. Lilienstern Graphische Darstellugen zur ältesten Geschichte und Geographie von Aethiopien und Aegypten (Berlin, 1827). Map No. 5